

# የጳውሎስ ሶስተኛው የሚሺነሪ ጉዞ

- ጳውሎስ በቆሮንቶስ በነበረበት ጊዜ ከአቂላና ከሚስቱ ጋር ገገናኝቶ ነበር። ልክ እንደጳውሎስ ድንኳን ሰፊዎች ስለነበሩም ከእነርሱ ጋር እየኖረ አብሯቸው ድንኳን ይሰፋ ነበር።እርሱ ከቆሮንቶስ ሲወጣም አብረውት ከእርሱ ጋር ሄዱ። ከቆሮንቶስ ከወጣ በኋላ በቀጥታ የሄደው ወደ ኤፌሶን ሲሆን ከዚያም ወደኢየሩሳሌም በመቀጠልም ወደአንፆኪያ ነበር። ከዚህ በኋላ ያደረገው ነገር ቢኖርም ከዚህ በፊት ባደረጋቸው የሚሺነሪ ጉዞዎቹ የተለወጡ ሰዎችን በያሉበት እየተዘዋወረ መጎብኘት ነበር።

- በኤፌሶን በነበረው ቆይታ ብዙ አስገራሚ ነገሮች ተከናውነዋል። አስራ ሁለት በመጥምቁ ዮሐንስ የተጠመቁ ሰዎችን አገኘና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ እንደሚገባቸው ነገራቸው። ይህንንም ፈቅደው አደረጉ። ጳውሎስም እጁን ጭኖ ፀለየላቸውና በሁሉም ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው። ልክ በጴንጤ ቆስጤ ቀን እንደሆነው እነዚህ ሰዎችም በተለያዩ ልሳኖች መናገር ጀመሩ።

- እንዲሁም ጳውሎስ በኤፌሶን በነበረበት ጊዜ ብዙ ተአምራት ተፈፀሙ። ጳውሎስ የነካቸው መሃረቦችን በድውያን ላይ ሲያደርጉም ሕመምተኞቹ መፈወስ ጀመሩ። እንዲሁም ርኩሳን መናፍስት ሰዎችን እየለቀቁ ይሄዱ ነበር።

ስለጳውሎስ ሶሰተኛ ሚሺነሪ ጉዞ በሐዋርያት ስራ ምዕራፍ 18፡18 እስከ ምዕራፍ 19፡22 ድረስ ባለው ክፍል ውስጥ ማንበብ ትችላላችሁ።